የሰ/መ/ቁ. 14981

ግንቦት 04 ቀን 1998 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሠ

አብዱልቃድር መሐመድ

ጌታቸው ምህረቱ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሒሩት መለሰ

**አመልካች** ፡- የኢትዮጵያ ልማት ባንክ

**ተጠሪ** ፡- ወ/ሮ ሃዋ መሐመድ

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የባለሙያ አስተያየት የመጨረሻ ማስረጃ (conclusive evidence) መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡

አመልካች ለም/ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ አቶ መሐመድ አብዱራህማን ከባንኩ ለወሰዱት ብድር ተጠሪ ንብረታቸውን በዋስትና ስላስያዙ ተበዳሪው በሚፈለግባቸው ዕዳ ተጠሪ በዋስትናቸው መሠረት ግዴታቸውን እንዲወጡ ጠይቋል፡፡ ተጠሪም የገቡት የዋስትና ውል አለመኖሩን በመግለጽ የተከራከሩ ሲሆን ፍ/ቤቱም በዋስትና ሠነዱ ላይ ያለው ፊርማ የተጠሪዋ አለመሆኑን በፖሊስ የቴክኒክ ምርመራ በመረጋገጡ ተጠሪ ሊጠየቁ አይችሉም በማለት ወስኗል፡፡ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ይግባኙን ባለመቀበል መዝገቡን ዘግቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም በባለሙያ የሚሰጥ አስተያየት የመጨረሻ ማስረጃ (conclusive evidence) ነው ወይ? የሚለውን የሕግ ነጥብ ለመመርመር ጉዳዩን ለሰበር ችሎት አስቀርቧል፡፡ ግራ ቀኙም ክርክራቸውን በጽሑፍ ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱም አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ ከተገቢው ሕግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

በዚህ መዝገብ ዋነኛው አከራካሪ የሆነው ተጠሪ ንብረታቸውን በማስያዝ የዋስትና ግዴታ የመግባታቸው ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች ተጠሪዋ ለተሰጠው ብድር የዋስትና ግዴታ መግባታቸውን ለማስረዳት የዋስትና ሠነዱን እንዲሁም ምስክሮችን አቅርቧል፡፡ ምስክሮቹም ተጠሪ በዋስትና ውሉ ላይ የፈረሙ ለመሆኑ ባል የሌላቸው መሆኑን ከቀበሌ ማስረጃ አቀርበው እንደነበር አረጋግጠዋል፡፡ ነገር ግን ተጠሪ ፊርማውን የካዱ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ፊርማው በፖሊስ የቴክኒክ ምርመራ ክፍል እንዲመረመር አድርጎ በሠነዱ ላይ ያለው ፊርማ የተጠሪዋ አለመሆኑን የሚያረጋግጥ ውጤት ለፍ/ቤቱ ቀርቧል፡፡ ፍ/ቤቱም ፊርማው የተጠሪ አለመሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ስለቀረበ የሰው ማስረጃው ፋይዳ ከሌለው መሠማታቸው ስህተት ነው በማለት የመስክሮቹን ቃል ሙሉ በሙሉ ውቅድ በማድረግ ተጠሪን ከተጠያቂነት ነፃ አድርጓቸዋል፡፡ በዚህም ምክንያት የባለሙያ አስተያየት ተቃራኒ ማስረጃ ሊቀርብበት የማይችል የመጨረሻ ማስረጃ መሆን አለመሆኑን መመርመሩ አስፈላጊ ነው፡፡

በአገራችን ራሱን የቻለ የማስረጃ ሕግ ባለመኖሩ በዚህ ጉዳይ በቀጥታ ተፈፃሚነት ያለው ድንጋጌ ሊጠቀስ ባይችልም በሌሎች አገሮች ተቀባይነት ካገኘው የማስረጃ ሕግ መርህ ግን መረዳት የሚቻለው የባለሙያ አስተያየት ብቻውን ለመቆም የሚችል ወይም በተቃራኒ ማስረጃ ሊስተባበል የማይችል ሳይሆን ይልቁንም ከሌሎች ማስረጃዎች ጋር ተገናዝቦ ብቃቱና ተአማኒነቱ ሊመዘን የሚገባ መሆኑን ነው፡፡ ምክንያቱም ምንም እንኳን በባለሙያ አስተያየቱ መሠረት የሚያቀርበው የሣይንሳዊ ጥናትና ምርመራ ውጤትን ቢሆንም ሣይንስ በራሱ ፍፁም እርግጠኛነት የሌለውና ሙሉ እምነት የሚጣልበት አይደለም፡፡ ይህም በመሆኑ የባለሙያ አስተያየት ብቻ እንደበቂ ማስረጃ ተቆጥሮ ሌሎች ማስረጃዎችን ያለበቂ ምክንያት ተቀባይነት ማሳጣቱ ወደ ተሣሣተ መደምደሚያ ሊያደርስ የሚችል ይሆናል፡፡

በተያያዘው ጉዳይም ቢሆን ፍ/ቤቱ የቀረበለትን የፖሊስ ምርመራ ውጤት ብቻ ተቀብሎ የምስክሮቹ ቃል ተቀባይነት ወይም ተአማኒነት ሊያጣ የሚገባበትን በቂ ምክንያት ሣይገልፁ የምርመራ ውጤቱ በመቅረቡ ብቻ በደፈናው የሰው ማስረጃ ፋይዳ የለውም በማለት የደረሰበት መደምደሚያ ስህተት መሆኑን ተረድተናል፡፡

በሌላ በኩል ፍ/ቤቱ ከግራ ቀኙ የቀረቡትን ማስረጃዎች እንዲሁም ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት ጠቃሚ ነው የሚለውን ማስረጃ አስቀርቦ መመርመር የሚችል ቢሆንም የጠሪን ምስክሮች እንዲቀርቡ በማድረግ የምስክርነት ቃላቸውን ከሰማ በኋላ የባለሙያ አስተያየት በመቅረቡ ብቻ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 207 መሠረት የምስክርነት ቃሉን ውድቅ ማድረጉ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን የተከተለ አካሄድ አልነበረም፡፡ ምክንያቱም የተጠቀሰው የሥነ-ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌ ከሥነ-ሥርዓት ውጪ ክስ ሲቀርብ ወይም በክሱ ውስጥ ከደንብ ውጪ የሆነ ተግባር ሲፈፀም ስህተቱን ለማረም የተቀመጠ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን ምስክሮቹ በአመልካቹ የተቆጠሩ በመሆናቸው ቀርበው መሰማታቸው ስህተት አልነበረም፡፡ በአመልካች ባይቆጠሩ እንኳን ፍ/ቤቱ ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት ጠቃሚ ናቸው ብሎ ካመነ እንዳይሰሙ የሚከለክል ሥርዓት የለም /የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 264 ይመለከቷል/፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቱ ምስክሮቹ የሰጡት ምስክርነት ተአማኒነት የለውም ካለ ይህንኑ ገልፆ ውድቅ ከሚያደርገው በቀር ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን የሥነ-ሥርዓት ድነጋጌ መሠረት በማድረግ የሰው ማስረጃውን ውድቅ ማድረጉ ስህተት ነው፡፡

በአጠቃላይ የስር ፍ/ቤቶች የባለሙያ አስተያየቱን እንደመጨረሻ ማስረጃ (conclusive evidence) አድርገው በመውሰድ የሰው ማስረጃውን ውድቅ በማድረጋቸው የሕግ ስህተት ፈጽመዋል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

3. የም/ሸዋ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 24190 ግንቦት 28/1995 የሰጠው ውሣኔ እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 00894 ታህሣስ 13/1996 የሰጠው ትዕዛዝ ተሽረዋል፡፡
4. ተጠሪ በዋስትና ባስያዙት ንብረት ግምት ልክ ለሚፈለገው የዕዳ መጠን ተጠያቂ ናቸው፡፡
5. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ በመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

/አተ